# ምስክር
# ጆርጅ ሀበሽ --የፍልስጤም ሕዝብ ትግል መሪ
# የኢትዮጵያም ትግል ወዳጅ

ባለፈው ሰሞን በፈረንጆች አቆጣጠር በጃንዋሪ 27 ጆርጅ ሀበሽ በልብ በሽታ የተነሳ በአማን (ጆርዳን) ሆስፒታል አርፎ በአማን የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብሯል። ሀበሽ በፍልስጤም ሕዝብ ተወዳጅ የነበር የትግል መሪ ስለነበር በሀኪምነቱ ብቻ ሳይሆን በአዋቂነቱም አልሀኪም የሚባል መጠሪያ ተሰጥቶት ነበር።

ጆርጅ ሀበሽ በሊዳ ሀተማ በፍልስጤም ከ80 ዓመት በፊት ተወልዶ እስራዔል ስትመሰረት ያው እንደሌሎቹ ፍልስጤሞች መሰደድ ነበረበት። በፈረንጆች አቆጣጠር በ1952 የአረብ ብሄረተኛ እንቅስቃሴ መስራች አባል ሆኖ ሲታገል ከቆየ በኋላ በ1968 ፒኤፍኤልፒ ወይም የፍልስጤም ነፃነት ሕዝባዊ ግንባርን አቋቁሞ ትግሉን አጧጡፏል። በመጀመሪያ ሀበሽ ብሄረተኛ ሆኖ በተለይም የግብፁን መሪ አብደል ናስርን መስመር ተከታይ ነበር። ግን ይህ ብሄረተኛ ርዕዮት የአረብን ሕዝብ ሆነ የፍልስጤምን ሕዝብ መሰረታዊ ችግር መፍትሄ ሊሰጥ አይችልም ብሎ በማመኑና የናስርም አገዛዝ አምባገነናዊ መሆኑን በመረዳቱ ወደ ማርክሳዊ ርዕዮት አማኝነት ተለውጦ በፅናት ከመታገሉ ሌላ ለዓለም ሕዝብ አብዮቶችም ቀጥተኛ እርዳታ ሲያደርግ ቆይቷል። ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞአችን በካይሮና አማን፤ በዳማስከስ ማለፍ አለበት ባዩ ሀበሽ የትግሉን ሀገሮች አቀፍ ይዘት ከተረዱት የመጀመሪያው ነበር። በዚህም መሰረት ኢሕአሠ ትግል ሲጀምር የጆርጅ ሀበሽ ድርጅት የመሳሪያና ጥይትም እርዳታ አድርጎለት እንደነበር መታወቅ ያለበት ታሪክ ነው። ይህን እርዳታ ለድርጅቱ ሲያደርግም በእከከኝ ልከክልህ መሰረት ኢሕአፓ ይህን ያደርግልኝ ብሎ የጠየቀው አንድም ነገር አልነበረም። የጆርጅ ሀበሽ ድርጅት በ1970ዎቹ አይሮፕላኖችን በመጥለፍና በተለይም ዓለም አቀፋዊ ዝናን ያተረፈችውን ታጋይ ላይላ ካሊድን በማሰለፍ ዕውቅናን ያገኘ ነበር። ጆርጅ ሀበሽ ከያሲር አራፋት፤ጆርጅ ሀዋትሜህና ሌሎች ጋር የፍልስጤም ነፃ አውጪ ድርጅትን (ፒኤልኦን) የመሰረተ ሲሆን የኦስሎን ስምምነትን መቸም ባይደግፍም፤ እስከ ዕለተ ሞቱ የትጥቅ ትግል ደጋፊ ቢሆንም ህይወቱ ስታልፍ የዛሬው የፍልስጤ ም መንግስት መሪ መህመድ አባስ ፍልስጤም ከጀግና ልጇ ተለየች ብሎ ሰንደቅ ዓላማ በሀዘን በግማሽእንዲሰቀል አዟል። ሀበሽ ወደ ትውልድ ሀገሩ ሳይመለስ ህይወ ቱ አልፋለች።

ጆርጅ ሀበሽ በርካታ የፖለቲካ ፅሁፎችን የፃፈ ምሁር ከመሆኑ ባሻገር ( ከመሞቱ ጥቂት ቀናት በፊት "አብዮተኞች አይሞቱም " የሚለው መፅሀፉ በፈረንሳይ ሀገር ታትሞ ወጥቷል) ከሕዝቡ ያልተለየ ፅኑ ታጋይ መሆኑን ታሪክ መስክሮለታል። አሜሪካ ሽብርተኛ ያለችው ይህ የፍልስጤም ጀግና በዓለም ጭቁኖች ሁሌም የሚታወስ ሲሆን ለኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ትግል ባደረገው እርዳታ ደግሞ የማንረሳው አብዮታዊ ነው።